## ላንባ እኔ ለእሳት ድንጋይ ለጥሩሩ!!

ከእቶን እሳት ተፈልጦ፤
እሳት እሳትን አምጦ፤
እሳት ብርሃንን ውጦ፤
እርቃኑን ቢቀር አጊጦ፤
ቢአየው አይኔ አፍጦ፤
እሳት አለብርሃን አጊጦ።

ንገረኛ የእሳት አምላክ፤
የገሃነም የእቶን ሽሪክ፤
አለብርሃን የተወዘፍክ፤
በአፈር በነጠላው የተሸፈንክ።
ምኑን ሳ'ትከው ተጎልተህ፤
ዝንተ ዓለም እቶን ሆነህ፤
ተቀምተህ ተወዝፈህ፤
ዛርህ ሲነግስ ተንዘፍዘፈህ፤
የእሳት እራት እሳት ሆነህ፤
በጨለማ በቶን እሳት ተውጠህ።
ከል ለብሰህ አለብርሃን ለቀረኸው፤
በድቅድቅ ጨለማ ለተዋብከው።

ላንባ እኔ ለእሳት ድንጋይ ለጥሩሩ፤
ላልቅስ እኔ ለሆድ አደር ለምሁሩ፤
በጨለማ እሳት ሆኖ አለብርሃን በመኖሩ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com